**በወንጌል የተገለጠው ፅድቅና**

**የአሁኑ ዘመን መከራ**

**የንባብ ክፍል**:- ሮሜ 8:18-27

**ዓላማ:-**

-በእምነት የፀደቁ አማኞች ከመከራ ነፃ አለመሆናቸውን ማሳሰብ።

- በእምነት የፀደቁ አማኞች ከአሁኑ ዘመን መከራ ይልቅ ተስፋቸው ላይ እንዲያተኩሩ ማሳሰብ።

- በእምነት የፀደቁ አማኞች በመከራ ውስጥ ሲያልፉ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸው ማረጋገጥ።

*መግቢያ:-* በቀደመው ትምህርት በእምነት የፀደቁ የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ ቅዱስ ስጋን የመግደል እዳ እንዳለባቸው፤ እንዲሁም በዚህ ምድር ምልልሳቸው በመንፈስ ቅዱስ በመመራት እንደሆነ እና ከክርስቶስ ጋር ወራሾች መሆናቸውን ተመከተናል። በዛሬው ትምህርት ደግሞ በእምነት የፀደቁ አማኞች የአሁኑን ዘመን መከራ እንዴት እንደሚያሸንፉትና በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሊኖራቸው ስለሚገባ መታመን እንማራለን።

**1: የፀደቁ አማኞች በአሁኑ ዘመን መከራ የሚቀበሉበት ምክንያት**

1:1 በዚህ በወደቀ ዓለም ውስጥ ስለሚኖሩ። **ዮሐ 16:33**

1:2 እምነታቸው ስለሚፈተን። **1 ጴጥ 1:6-7**

1:3 የክርስቶስ አገልጋዮች ስለሆኑ። **2ቆር 11:22-29**

1:4 በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ስለሚኖሩ። **ማቴ 24:9-25**

**2: አማኞች የሚንቁበት ምክንያቶች። ሮሜ 8:19-25**

2:1 ሊገለጥላቸው ያለው ክብር ታላቅ ስለሆነ።

2:2 የሰውነታቸው ቤዛ የሆነውን ልጅነት ተስፋ ስለሚያደርጉ።

2:3 የእግዚአብሔር ልጅነት ደረጃዎች:-

2:3:1 በእግዚአብሔር ሀሳብ አስቀድሞ መወሰን። **ኤፌ 1:5**

2:3:2 አሁን ያገኘነውና የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን የተቆጠርንበት። ገላቲ **3:26 ሮሜ 8:14**

2:3:3 በክርስቶስ. ያገኘነውን ውርስ ሙሉ በሙሉ የምንረዳበት። **ሮሜ 8:23**

2:4ተስፋቸውን ለመያዝ በመንፈስ ቅዱስ ስለሚ,ቃትቱ።

**3: የመንፈስ ቅዱስ ስራ እማኞች በመከራ ሲልፉ**

3:1 በድካማቸው ያግዛቸዋል።

3:2 ስለ እነርሱ ይቃትታል/ይማልዳል።

3:3 የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያስታውቃቸዋል።

*ማጠቃለያ:-* አማኞች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከመከራ ነፃ እንደሚሆኑ መፀሀፍ ቅዱስ አያስተምርም። ነገር ግን በመከራ እንዳይሸነፉ ማድረግ ያለባቸውን ያሳስባቸዋል።በዚህ መሰረት ዛሬ በተለያየ  መከራ ውስጥ የምናልፍ አማኞች በመከራችን

ላይ ሳይሆን ትኩረታችን በተስፋችን ላይ እናድርግ ። ያኔ መከራችን ይሸነፋል።ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንታመን እርሱ ስለኛ ይማልዳልና። ለኛ ሊገለጥ ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን የአሁን ዘመን ስቃይ ምንም አይደለም!!!!